# አሁንም የማስጠንቀቂያ ደወል!
# አማራ ሆይ ከአሲራውያን ውድቀት ተማር!

*በበላይነህ አባተ abatebelai@yahoo.com*

የአማራ ዘር ፍጅትና ማጥዳት ካለፉት ሰላሳ ዓመታት በከፋ ሁኔታ ቀጥሏል፡፡ የአማራ እናቶች፣ አባቶችና ልጆች በአበዱ አውሬቾች ሲታረዱ፣ ሲገነጠሉና ሲጎተቱ ማየት እንኳን ደማቸውን የሚጠጣው የኢትዮጵያ ምድር ተላይ የሚመለከተውን የኢትዮጵያ ሰማይም ሰልችቶታል፡፡

እነዚህ ያበዱ አውሬዎቾ ህሊናና የሚያስብ አይምሮ ያላቸው ይመሰል ድስኩራሙ ምሁርም “መጀመርያ ሰው ነኝ ተዚያም ኢትዮጵያዊ እያለ!” ተዳር ቆሞ አማራን በድስኩር ገመድ እያስጠለፈ ያሳርዳል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ የማያባራ የአድርባይዎች ድስኩር “ነፍጠኛን እረድ፣ አማራን አባር!” ለሚል ያበደ ውሻ፣ ጅብ፣ ዘንዶና እባብ እንዴት ሊገባው ይችላል? “መጀመሪያ ሰው ነኝ ተዚያም ኢትዮጵያዊ!” የሚለው ለአምሳ ዓመት ፍሬ ያላፈራ ወሸላ ድስኩር ዓይኑን አፍጦ አማራን ሊውጥ የመጣን ጅብ እንዴት ርህራሄ ሊዘራበት ይችላል?

አማራ ሆይ! ዘርህ እንዳይጠፋና አገር አልባ ተመሆን ለመዳን ተአሲሪያውያን ውድቀት ትምህርት ቀስመህ ያያቶችህን ቀበቶ እንደገና መታጠቅ ይኖርብሃል፡፡

አሲሪያውያን ከ900-600 ዓመተ አለም ለ300 ዓመታት በዓለም ላይ ጠንካራውንና




ኃያሉን መንግስት የመሰረቱ ሕዝብ ነበሩ፡፡ ኃያሉ መንግስታቸው በአሁኑ አጠራር ከኢራን እስከ ግብፅ አልፎም እስከ ቱርክ ያለውን ግዛት ያስተዳድር ነበር፡፡ [1]

በዚያን ዘመን አሲራውያንን ለኃያልነት ያበቃቸው የቦካው ባህላቸው፣ የሥነ-ጽሑፍ፣ የትምህርትና የህክምና ጥበባቸው ነበር፡፡ በባህልና በጥበብ በመዳበራቸውም በሰው ልጅ ታሪክ ለመጀመርያ ጊዜ ከብረትና ከነሐስ የጦር መሳሪያ ሰርተው ዘመናዊ መከላከያ የመሰረቱ ጀግናና ፋኖ ሕዝብ ነበሩ፡፡ [1]

የአሲሪያውያን የአስተዳደር፣ የሥነ-ጽሑፍና የጥበብ ቋንቋ አረማያ ነበር፡፡ [2]አረማያ እየሱስ ክርስቶስ በሰውነቱ ይናገረው የነበረው ቋንቋ ነበር፡፡ እንደ አማራ ሁሉ የአሲሪያውያን የመጀመርያው የአንድ አምላክ አምልኮታቸው የተመሰረተውም በብሉ ኪዳን ነበር፡፡ የመጀመርያው ክርስትያን የአሲሪያን መሪም በራሱ በክርስቶስ ስብከት ክርስትያን እንደሆነ ይነገራል፡፡

የአረማያ ቋንቋ ከአማርኛ ጋር ይመሳሰላል፡፡ እንዲያውም የዘመኑ አሲሪያውያን አማርኛን የአራማይክ እህት ቋንቋ ሲሉ ይጠሩታል፡፡ [2]

አሲሪያውያን በቦካው ባህላቸው፣ በሥነ-ጽሑፋቸው፣ በጥበባቸውና በጠንካራ መሪዎቻቸው ምክንያት ለ300 ዓመታት ገናና ሆነው ቆይተዋል፡፡ ከ300 ዓመታት በኋላ ግን እርስ በርሳቸው መነታረክና መዋጋት ሲጀምሩ ኃይላቸው እንደተዳከመ ታሪክ ያወሳል፡፡ ይህ የአሲሪያውያን የእርስ በርስ ብጥብጥ ከአረቢያ ሰርጥ ለፈለሱና በናቡከደናጦር አባት ለሚመሩት ቻሊዳውያን ጥሩ አጋጣሚ ሆነላቸውና ገናናውን የአሲርያ መንግስት አስወግደው የባቢሎንን መንግስት እንደ ገነቡ ተጥፏል፡፡ [3-5] የባቢሎን መንግስትም በፈንታው በፔርሻውያን መንግስታት ድምጥማጡ እንደጠፋ ይታወቃል፡፡

በራሳቸው የእርስ በርስ ብጥብጥ ምክንያት ባጃሊዲያን ክብራቸውን የተነፈጉት አሲሪያን ከ600 አመተ ዓለም ጀምሮ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጥዳት ወንጀል ስልተፈጸመባቸው ዛሬ እንኳን አገር ሊኖራቸው በመጥፋት ላይ ካሉት የሰው ዘሮች ተቆጥረዋል፡፡ [3] እየሱስ ክርስቶስ በምድር ሳለ ይግባባበት የነበረው የማርኛው እህት አራማያ ቋንቋ ዛሬ እንደ ግእዝና ኮብቲክ የቤተ ክርስትያን ቋንቋ ብቻ ሆኗል፡፡ [3]

አማራ ሆይ! ራስህን አደራጅተህ እንደ አያቶችህ እጣ ፈንታህን በጥበብህና በክንድህ ታልወሰንከው ዛሬ እየሄድክበት ያለው መንገድ የአሲሪያውያን መንገድ ይመስላል፡፡ በአለፉት ሰላሳ ዓመታት ግብር እየከፈልክ የምታስተዳድራቸው ገዥዎችና የሕዝብ መገናኛዎች በቦካ ባህልህ፣ በሃይማኖትህ፣ በሥነ-ጽሑፉህ፣ በታሪክህ፣ በቅርስህና በስብእናህ ያለማቋረጥ ዘምተውብሃል፡፡ ትዕግስትህ መጥፊያህ ሆኗል፡፡ ራስህንም ሆነ ኢትዮጵያን ለማዳን የራስህ መጠንከር ወሳኝ መሆኑን ተአያቶችህ ተሞክሮ መማር የተሳነህ ይመስላል፡፡

ባህልህን፣ ታሪክህን፣ ሃይማኖትህን፣ ቅርስህንና ሥነ-ጽሑፉን ያዳከመው የወሮበሎች ቁማር ዛሬ ደግሞ አካልህን አያረደ የኢትዮጵያን ምድር በደምህ እያጠበ ይገኛል፡፡

አማራ ሆይ ከመጥፋት ወይም አገር አልባ ከመሆንህ በፊት ከአሲሪያውያን ከፍተኛ ውድቀት ተምረህ የሚከተሉትን እርምጃዎች በአስቸኳይ መውሰድ ይኖርብሃል፡

1 መንግስት አልባ መሆንህንና እንደ ጠላት የሚቆጥሩህ ሊያጠፉትህ በየእለቱ ቁማር እየቆመሩ መሆኑን መገንዘብ
2 ብአዴን የሚባለው እርጉምና ባንዳ ልጅህ አማራን የማጥፋቱ ቁማር መጫዋቻ ካርታ መሆኑን ተገንዝበህ እንደ ታሪክህና እንደ ባህልህ የጎበዝ አለቃዎችህን መርጠህ ህልውናህን ለማዳን በየጎራው መንቀሳቀስ
3 መደራጀት፤ መደራጀት፤ መደራጀት አሁም መደራጀት

4 ጨርሶ ሊውጥህ የመጣን የድንጋይ ዘመን ጅብ በአንድነት መክተህ መከላከል እንጅ እርስ በርስ መናከስህን በአስቸኳይ ማቆም
5 ጅብ ታፋቸውን እየዘነጠላቸው ሳለ እንደ ሰባራ አህያ በየሰፈሩ እየተልከሰከሱ የኀጠኝነት መንፈስን የሚያናፍሱትን የቀድሞም ሆነ የአሁን የብአዴን ካድሬዎች በምክርም ሆነ በተግሳፅ ማስቆም
6 ባህልህን በተለይም ሰምና ወርቅ ዘፈኖችህ፣ ቀረርቶህ፣ ፉከራህ፤ ዋሽንትህ፣ ክራርህና መሰንቆህ የጀግና መፍለቂያ ባህሮች መሆናቸውን ተገንዝበህ እንደ ጥንቱ ማጎልበት፤ ልጆችህንም በዚህ ባህል ማሳ ውስጥ ማሳደግ
7 ኢትዮጵያ እምትድነው አንተ አማራው ግዛትህ ከእየሩሳሌም እስክ ማደጋስካር ተገንዝበህ ግዛትህን ለማስጠበቅ ተደራጅተህና ቆርጥህ ስትነሳ እንጅ ሊያጠፉህ የፈጠራ ታሪክ የጫሩትን ጭራቆች በመለመንና በመለማመጥ አለመሆኑን መረዳት
8 አንተን የማዳከሙና የማጥፋቱ ቅዣት ከክርስቶስ ዳምግም ምጣት በኋላም የማይጠፋ መሆኑን ተገንዝበህ ዳግመኛ በእስስቶች ላለመታለልና የቁማር መጫወቻ ላለመሆን እንደ አያቶችህ በጥበብና በንቃት መጠበቅ
9 እንኳን ሰው ትንኝም ዘሩ እንዳይጠፋ ይታገላልና በዓለም ላይ የተበተንክ አማራ ዘርህ እንዳይጠፋና አገር አልባ እንዳትሆን በምትችውለው መንገድ ሁሉ መታገል
10 ከሶስት ሺ ዓመታት በፊት በዓለም ገናና የነበሩት አሲሪያውያን ዛሬ አገር አልባ የሆኑበት ምክንያት እርስ በርስ በመናከሳቸውና ባለመደራጀታቸው መሆኑ ተገንዝበህ ገመድ ጉታታውን አቁመህ ህልውናንህንና አገርህን ላለማጣት ከአድዋው የነፃነት ዘመቻም በበለጠ ተደራጅተህ ራስህን መከላከል

አማራ ሆይ! በአሲሪያውያን የደረሰው አገር አልባነትና የዘር መጥፋት በአንተ ላይም ተጧጡፏል፡፡ ይህ አማራን አገር አልባ የማድረግና የማጥፋት ወንጀል ዳር ደርሶ አማራ አገር አልባ ከመሆኑ በፊት ሁሉም አማራ በሚችለው መንገድ መታገል ይኖርበታል፡፡

አማራ ሆይ! ለሰላሳ ዓመታት አማራን ለማጥፋት የተኪያሄደው ዘመቻ ተጧጡፎ አማራ በመላ አገሪቱ እየታረደ ባለበት ወቅት እንዳትደራጅ ለአምሳ ዓመት ፍሬ ባላፈራ ድስኩር የሚሸብቡህን ሆዳምና ድስኩራም ምሁራን በቃ ልትላቸው ይገባል፡፡ እነዚህ ጣት አፍተልተይ አድርባይ ምሁራን አንተን አማራውን እንደ አሲርያውያን አማርኛህንም እንደ አራማያ ለማጥፋት በሚደረተረው ሸርና በሚቆመረው ቁማር በተዘዋዋሪ ተሳታፊ በመሆናቸው ወግድ ልትላቸው ይገባል፡፡

አማራ ሆይ! አሲሪያውያን ከደረሱበት ደርጃ እንደርስም በሚል ሳትደራጅና ራስህን ሳትከላከል ቀርተህ አገር አልባ ስትሆን ከአምሳ ዓመታት በኋላ ይኸንን ጽሑፍ ብታነበው ምይ ይጠቅምሃል?

አማራ ሆይ! እየበላህ ያለው ጅብ ስብከት፣ ልመና፣ ሰብአዊነትም ሆነ ድስኩር የማይሰማ፣ ቢሰማም የማይገባው፣ ቢገባውም የማይቀበል ያበደ አውሬ መሆኑን ልትገነዘብ ይገባል፡፡ ይኸንን የምትከላከለውና እንደ አሲሪያውያን አገር አልባ ተመሆንና ተመጥፋት የምትተረፈው እንደ አያቶችህ በጎበዝ አለቃህ ተደራጅተህ ስትከላከል ብቻ መሆኑን ልታጤን ይገባል፡፡

አመሰግናለሁ፡፡

***End notes:***


1. Assyrian Empire: The Most Powerful Empire in the World : The History Net. (accessed in September, 2020) https://www.historyonthenet.com/assyrian-empire-the-most-powerful-empire-in-the-world
2. Modern Aramaic, Assyrians/Syriac , Nocolas Awede et al
3. Revival, genocide and survival, Modern Aramaic, Nicolas Awede et al page 9
4. The Fall of the Neo-Assyrian Empire 630-609 BC http://cdli.ox.ac.uk/wiki/doku.php?id=the_fall_of_the_neo-assyrian_empire_630-609_bce ((accessed in September, 2020)
5. Ancietn Jewish History: Virtual Jewish Library https://www.jewishvirtuallibrary.org/the-chaldeans-612-539bce ((accessed in September, 2020)
6. The Chaledians Empire: The latin Library http://www.thelatinlibrary.com/imperialism/notes/chaldean.html (accessed in September, 2020)
7. The Chaledians_ New Babyloneans http://www.sussexvt.k12.de.us/science/The%20History%20of%20the%20World%20Secrets%20of%20the%20Ancient%20Past/Mesopotamia/The%20Chaldeans.htm (accessed in September, 2020)


*መስከረም ሁለት ሺ አስራ ሶስት ሺህ ዓ.ም.*